**CALGARY ETHIOPIAN COMMUNITY ASSOCIATION**

**በካልጋሪ የኢትዮጵያ ኮምዩኒቲ ማሕበር**

# ሕብረት

**“Hibret”, Monthly Newsletter**

ወርሃዊ ጋዜጣ

ቅጽ ፭ ቁጥር ፫ ኅዳር ፲፱፻፺፯

**Volume 5 Issue 3**
**November 2004**

***In this Issue***

| | |
|---|---|
| በደቡብ ኮሪያ ለኢትዮጵያ | 2 |
| Kenya toasts | 2 |
| በስዊዝ ኢትዮጵያውያን | 3 |
| አውስትራሊያ ከኢትዮጵያ | 3 |
| ኢትዮጵያ በሶማሊያ | 3 |
| ብራድ ፒት ለኤድስ | 3 |
| ኢትዮ-ኬኒያ ድንበር | 3 |
| New cave Found | 4 |
| Encyclopaedia Ethiop | 5 |
| ይድነቃቸው ተሰማ | 5 |
| □□□ወ□□ | 6 |

## የአማርኛ ፊደል ለሞባይል ቴሌፎን አገልግሎት ሊውል ነው

ረዥም ታሪክ ያለው የአማርኛ ፊደል በሞባይል ሴልፎን ተቀርጾ አማርኛን ማንበብና መጻፍ ለሚችሉ አገልግሎት እንዲሰጥ ለማድረግ መታቀዱን አሶሺየትድ ፕሬስ ዘገበ፡ይህን ከፍተኛ የምህንድስና እውቀት የሚጠይቀውን ተግባር ያከናወኑት አሜሪካ ውስጥ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ሣይንቲስቶች መሆናቸውን ዜናው ገልጿል፡የምርምር ሃሳቡ አመንጪ የሆኑትን ኢንጂነር ሳሙኤል ክንዴን ዋቢ በማድረግ ዜናው እንደዘገበው ከአራተኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ለረዥም ምዕተ ዓመታት በሥራ ላይ የዋለውን አማርኛ ከዘመኑ ሽቦ አልባ መገናኛ ሞባይል ላይ በማዋሃድ በሥራ ላይ ለማዋል ተችሏል፡በመላው ዓለም የአማርኛ ፊደል ተጠቃሚ ኢትዮጵያውያን ሕዝቦች ቁጥር ቀላል አለመሆኑን የጠቆሙት ፕሮፌሰር ኢንጂነር ሳሙኤል የሞባይል አማራች ፋብሪካዎችንም በቀላል ዋጋ ለገበያ ለማቅረብ መልካም የገበያ አጋጣሚ እንደሚፈጥርላቸው አብራርተዋል፡ከአፍሪካ የራሷ ፊደል ያላት ብቸኛ አገር ኢትዮጵያ መሆኗን የጠቆመው ዘገባው፤ ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ በጥቅም ላይ ያለው አማርኛ እንደሆነ ዘገባው አመልክቷል፡

## ኢትዮጵያ እና ሱዳን ድንበሮቻቸውን ለማካለል ተስማሙ

ኢትዮጵያን እና ሱዳን ለአዋሳኝ ድንበሮቻቸው የካርታ ማመላከት ስምምነት አጠናቀው በመሬት ላይ ለማካለል ዓለም አቀፍ እርዳታ እየጠበቁ መሆኑን ክቡር አምባሳደር ኡስማን ኤልሰኢድ ፋደል ኤልሲድ ገለፁ፡ የሱዳኑ አምባሳደር ከሪፖርተር ጋዜጣ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ እንዳስታወቁት ኢትዮጵያ እና ሱዳን ድንበሮቻቸውን በሚመለከት ሦስት ኮሚቴዎች ማለትም የአጠቃላይ ጉዳይ ኮሚቴ፣ የቴክኒክ ኮሚቴ እና ልዩ ኮሚቴ አቋቁመው ሥራዎች ሲያከናውኑ ቆይተዋል፡ የኢትዮጵያ እና የሱዳን የአዋሳኝ ድንበር ካርታዎች አንድ ዓይነት በመሆናቸው ምንም ዓይነት ችግር የለም ያሉት አምባሳደሩ ሆኖም «ጥቂት ስግብግብ» ያሏቸው የሁለቱ አገሮች የድንበር አዋሳኝ አካባቢ ነዋሪ ገበሬዎች አልፎ አልፎ ችግር እንደሚፈጥሩ ጠቁመዋል፡
በአሁኑ ሰዓት ሁለቱ አገሮች በካርታ የተስማሙትን 1600 ኪሎ ሜትር በመሬት ላይ ለማካለል ወጪው ከፍተኛ በመሆኑ ዓለም አቀፍ ተቋማት የፋይናንስ ድጋፍ እንዲያደርጉ የሁለቱ አገራት የውጪ ጉዳይ ሚኒስትሮች በጋራ መጠየቃቸውን አምባሳደር ኡስማን አመልክተዋል፡
የኢሕአዴግ መንግስት ሁመራን ለሱዳን መንግስት ሰጠ የሚል ፅሁፍ ማንበባቸውን የጠቀሱት አምባሳደሩ ይኸ ፈፅሞ ውሸት ነው፣ የሱዳን መንግስትም ሆነ ሕዝብ በሁመራ ጉዳይ የይገባኛል ጥያቄ የላቸውም በማለት አስተባብለዋል፡ አምባሳደር ኡስማን አያይዘውም «ለድንበር ማካለሉ ገንዘብ ከውጪ ሀገር እንኳን ባናገኝ ሁለቱ አገሮች በራሳቸው ያደርጉታል፤ ይህን አሁን ካላደረጉት ምንጊዜም ሊያከናውኑት አይችሉም ይሆናል» ሲሉ ተናግረዋል፡
የኢሕአዴግ መንግስት በድንበር ጉዳይ ከሱዳን ጋር ቁጭ ብሎ ለመነጋገር የፈቀደ በኢትዮጵያ የመጀመሪያው መንግስት መሆኑን አምባሳደሩ ጠቅሰው በሌሎችም ክልላዊና ዓለም አቀፋዊ የሁለትዮሽ የላቀ ግንኙነት መመስረቱን አስረድተዋል፡

## Mandela out to get his name back

Lawyers for Nelson Mandela's foundation have warned commercial companies to stop using the revered leader's namAbout 200 firms have sprung up with names like Nelson Mandela Panel Beaters and Nelson Mandela Fine Art, which have no

connections with the man. His famous prison number, 46664, has also been used by companies. But the Nelson Mandela Foundation is seeking to register exclusive

**Mandela**

rights to
both name and number, for use in its charitable campaigns. Trademark registration could take up to three years, but in the meantime the foundation has approached the 200-odd companies in South Africa using the Mandela name. "We have written letters to all of them asking them to drop the Mandela name," Tim Scholtz, chief operating officer of the foundation, told BBC News.

**'Commercial opportunity'**

He said it was the bigger companies they were keenest to chase. "Where a

*(Continued on page 3)*

### *ንግድ ለመጀመር ቢሮክራሲውን በማላላት ኢትዮጵያ ከደሀ አገሮች ከፍተኛውን ውጤት አስመዘገበች*

የዓለም ባንክ፣ የኢንተርናሽናል ፋይናንስ ኮርፖሬሽንና የኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ በቅርቡ በጋራ ለህትመት ያበቁት Doing Business in 2005, Removing Ostacles to Growth የሚለው የህትመት ውጤት በአለም አቀፉ የልማት እርዳታ ድርጅት (IDA) ከሚታገዙ ከሳህራ በታች ካሉ ሀገሮች መካከል አንድን ንግድ ለመጀመር የሚወስደውን ጊዜና መመሪያዎች በማቃለል ደረጃ በወሰዱት የማስተካከያ እርምጃ (reform) ኢትዮጵያ ቀዳሚውን ስፍራ እንደምትይዝ፣ በተመሳሳይ ከሰለጠኑት ሀገሮች ፈረንሳይ የመጀመሪያው ደረጃ ለመያዝ መብቃቷን አመለከተ፡

(Continued on page 2)

## ብእር ሲኮረኩር

*ሀበሾች ይኑሩ*

*ይኑር ሀበሻዬ የድንበር መደፈር የሀ*
*ገሩን መወረር*
*ወሬውን ሲሰማ*
*ለመሰለው ሀገር አርማና ባንዲራ*
*ላፈቀረው ታሪክ በክብሩ ሊኮራ*
*ያለውን ነፃነት*
*ለአናስነካም ማለት*
*እያንዳንዱ ራሱን ለክብሩ ሊሰዋ*
*ለታጠቀ ጠላት አልገብርም ብሎ*
*ሲቀላ ሲቀላ*
*ሕግ ልማድ ጥሶ የሰው ልጅን ኑሮ*
*በትዕቢት ሊወርረው የመጣበት ጠላ*
*ት*
*እስካፍንጫው ታጥቆ*
*አፍሮና ተዋርዶ ሲመለስ አይቼ*
*«እሰይ ጀግኔ!!!» የምለው*
*እንዲኖረኝ ብቻ*
*ይኑረው ሃበሻ፡*

*-በፈቃደ አዘዘ*

"አውራ ዶሮ በራሱ ቆጥ ላይ ጌታ ነው"

## ርእሰ አንቀጽ Editorial

በኦክቶበር 31 ቀን 2004 በተካሄደው የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ጠቅላላ ጉባዔ፤ ምልዓተ ጉባዔ የአባላት ሃምሳ አንድ በመቶ መሆኑ ቀርቶ አጠቃላይ ጉባዔ በተገኙ አባላት በድምፅ ብልጫ ውሳኔዎችን ማሳለፍ እንዲችል ለማድረግ የስራ አስፈፃሚው ኮሚቴ የህገ ማህበር ማሻሻያ ሃሳብ አቅርቦ እንደነበር የሚታወስ ነው፡፡ይህ የማሻሻያ ሃሳብ የቀረበበት ምክንያት እስከዛሬ እንደሚታየው በአጠቃላይ ጉባዔዎች ላይ የሚገኙ አባላት ቁጥር ዝቅተኛ በመሆኑ ምልዓተ ጉባዔውን ለማሟላት አስቸጋሪ ሆኖ በመገኘቱ ነው፡፡

ሆኖም የቀረበው የማሻሻያ ሃሳብ በጠቅላላ ጉባዔው ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቶ በምትኩ የጠቅላላ ጉባዔ ምልዓተ ጉባዔ ከአባላት ሃያ አምስት በመቶ እንዲሆን ጉባዔው ወስኗል፡፡ የስራ አስፈፃሚኮሚቴው ወደፊት በሚደረጉ ጠቅላላ ጉባዔዎች የአባላትን ተሳትፎ ለማሳደግና ምልዓተ ጉባዔውም መሟላቱን ለማረጋገጥ አስፈላጊውን ሁሉ ጥረት ያደርጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም አባላት ጠቅላላ ጉባዔ ላይ በመገኘት የሚያደርጉትን ተሳትፎ ማህበሩ በሚሰጣቸው ማናቸውም ግልጋሎቶችተጠቃሚ ለመሆን በዋነኛ መመዘኛነት ማየት መጀመር አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከዚህ አኳያ አባላት በማህበሩ ያላቸውን ተሳትፎ ለማሳደግ የማህበሩ አባል የሆኑት አቶ ሙሉጌታ ገላው ለችግሩ መፍትሄ ለማግኘት ይረዳ ዘንድ አንድ የጥናት ቅኝት (ሰርቬይ) ለማድረግ በዝግጅት ላይ ይገኛሉ፡፡ የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው አቶ ሙሉጌታንና ተባባሪዎቻቸውን በራስ አነሳሽነት ለማህበሩ ሊያደርጉ ላሰቡት አስተዋፅኦ በአባላት ስም እያመሰገነ፤ አባላትም ለጥናቱ አስፈላጊውን ትብብር እንድታደርጉ ይጠይቃል፡፡

በመጨረሻም መጪዎቹ የበዓላት ወራት የጤንነት፤ የሰላምና የብልፅግና እንዲሆኑላችሁ ልባዊ ምኞታችንን እንገልፃለን፡፡

## በደቡብ ኮሪያ ለኢትዮጵያ የእርዳታ ማሰባሰብያ ኮንሰርት ሊካሄድ ነው

ለኢትዮጵያ አምቡላንሶችና የእሳት አደጋ መከላከያ መኪናዎች ለመግዛት የሚውል የገንዘብ ማሰባሰብያ የሙዚቃ ኮንሰርት በደቡብ ኮሪያ፥ ቸንቺዮን ከተማ በዚህ ወር መጨረሻ እንደሚደረግ አዘጋጆቹ በትላንትናው ዕለት ገለፁ፡
«My Friend Ethiopia»(ወዳጄ ኢትዮጵያ)የተሰኘው የእርዳታ ማሰባሰብያ ኮንሰርት በቸንቺዮን ከተማ መስተዳድር፥ በኮሪያ የኢትዮጵያ ዘማች ወታደሮች ድጋፍ አድራጊና በሌሎች በርካታ በጎ አድራጊ ድርጅቶች እንደሚዘጋጅ ታውቋል፡
የዛሬ 54 ዓመት ወደ ኮሪያ ከዘመቱት ኢትዮጵያውያን ወታደሮች መካከል ከ 600 በላይ የሚሆኑት በቸንቺዮን ከተማ አካባቢ መሞታቸው ወይም መቁሰላቸው የሚታወቅ ሲሆን ወደ ኮሪያ የዘመቱ 6 ሺህ አፍሪካውያንን ለመዘከር ባለፈው ዓመት የቸንቺዮ ከተማ ከአዲስ አበባ ከተማ ጋር የእህትማማች ከተሞች ግንኙነት መመስረቷ ይታወሳል፡

**International Relations of Ethiopia: The Strategy of a Developing State**
By **Peter Both** (Calgary)
To Order contact: Authorhouse.com or Call Ted Jebb @ (403) 283 0900
Address: 210, 1220 Kensington Rd. NW
OR
**Call Peter at 540 -8035**

## የ 2004 የካልጋሪ ኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማህበር ስኮላርሺፕ አሸናፊዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. ሣራ ስለወንድም
2. ወርቅአገኘሁ ብስራት

## Kenya toasts US senator's victory

The Kenyan family of Barack Obama - the only black person to be elected to the US Senate in 2004 - are celebrating his victory in the state of Illinois
The son of a Kenyan father and American mother, Mr Obama won his seat after defeating a black Republican. His family stayed up all night in Nyanza province in western Kenya to follow the election results. "I am so, so happy," his grandmother Sarah said. His uncle said he hoped his nephew could improve their life.

### Obama beer

"It means a lot. Barack loves this family and I believe he's going to try hard to uplift the standards of life of the family here," Mr Obama's uncle Said Hussein Obama told the BBC's Network Africa programme Villagers of Nyangoma Kogalo, near the shores of Lake Victoria, have been looking forward to Mr Obama's victory for a very long time, he said. He said Kenya had a problem getting aid, but he hoped his country would now have a voice at the heart of the American government. "We're so happy that we have got somebody there who can actually identify with the problems of Kenya and the third world at large." Kenyan Vice-President Moody Awori said Mr Obama's victory had lifted his spirits. "[His win] in a way brings back the belief that in America, anyone can get to the top if one works hard." According to the BBC's Muliro Telewa in Nyangoma Kogalo, a local beer called Senator has been nicknamed "Obama" in honour of the Illinois politician. Barack Obama, who last visited his Kenyan home in 1992, is regarded as a potential presidential candidate. Americans have not elected a black president so far. Mr Awori also expressed the fear that there would be more extremism in the world - if President Bush was re-elected. Speaking to reporters in Nairobi. Mr Awori also said that he still expected America to be inward-looking and ignore the lot of developing countries even if Mr Bush's rival, John Kerry, won. But, Mr Awori stressed that these were his own views and not those of the Kenyan government.

## CECA'S CORNER

- Our regular **office hours** are:
  - **Mondays & Fridays: 6 to 9 pm**
  - **Saturdays: 9 am to 6 pm**
- We have new phone **(262 7260)** and fax **(262 9135)** numbers for our office. Please use this for any communication.
- Please send us your new babies & Wedding announcements as well as new graduates.
- Update your address with us. It is the most important information we need for effective communication with you.
- Please remember to send your membership dues.
- Send your suggestions for new project ideas to the CECA Executive Committee. **P.O.Box 22050, Bankers Hall, T2P 4J1**

## *Congratulations*

Baby Saron of Genet & Tesfaye



May you grow to make us all proud

### *ንግድ ለመጀመር ....*

የመጀመሪያው ደረጃ ለመያዝ መብቃቷን አመለከተ፡ይኸው በቅርቡ ለህትመት የበቃው መረጃ እንዳመለከተው በደሃ አገሮች የታየው የማስተካከያ ለውጥ የመጣው የተለያዩ መንግስታትና ለጋሽ ሀገሮች እርዳታ የሚያመጣውን ለውጥ በቁጥር ለመተርጎም ከመሞከራቸው ጋር እና ለነዚሁ ሀገሮች የሚውለው እርዳታ ባሳዩት ለውጥ መጠን መሆን አለበት ከሚለው እርምጃ ጋር የተያያዘ መሆኑን አመልክቷል፡ ይኸው የህትመት ውጤት በኢትዮጵያ አንድን ንግድ ለመጀመር (business start up) ይወሰድ የነበረው ጊዜና መመሪያዎች (ሂደቶች) በሚያበረታታ ሁኔታ መቀረፍ መቻሉን ሲያሳይ የውጭ ባለሃብቶች በኢትዮጵያ ስራ ለመጀመር በተዘጋ የሂሳብ ደብተር (blocked account) ማስያዝ ያለባቸው ገንዘብ ከሌሎች በተመሳሳይ ደረጃ ከሚገኙ ሀገሮች ጋር ሲተያዩ በመጠን የበዛ መሆኑን ገልጿል፡ ይኸው በንግድ እንቅስቃሴ ላይ ያሉ ቁጥጥሮችን በመለኪያ (በቁጥር) ለማስቀመጥ የሞከረው ለየት ያለ የንግድ እንቅስቃሴ መለኪያ የያዘው ህትመት በኢትዮጵያ ከንግድ እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ ያለውን የቁጥጥር ሂደት መሻሻል ሲያበረታታ፥ በአንፃሩ የመጨረሻ ደሀ ሀገሮች የሚባሉትን ጨምሮ በጠቅላላው ከተወሰዱ 145 ሀገሮች ውስጥ የኢትዮጵያ የነፍስ ወከፍ ገቢ በአመት 90 ዶላር መሆኑና ይህም ከጠቅላላው ከተመረጡት ሀገሮች የመጨረሻው ደረጃ መሆኑን አሳይቷል፡በዚሁ ህትመት እንደተካተተው ኖርዌይ በ 43,350 ዶላር የነፍስ ወከፍ ገቢ የመጀመሪያውን ደረጃ፥ ስዊዘርላንድ በ 39,880 ዶላር ሁለተኛ ደረጃ፥ አሜሪካ በ 37,610 ዶላር ሶስተኛውን ደረጃ ለመያዝ መብቃታቸው ተመልክቷል፡ በአንፃሩ በ 90 ዶላር ዝቅተኛውና የመጨረሻውን ደረጃ ኢትዮጵያ፥ በመቀጠል ብሩንዲና የኮንጎ ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ እያንዳንዳቸው በ 100 ዶላር ሁለተኛውን ዝቅተኛ ደረጃ፥ ሴራሊዮን በ 150 ዶላር ዝቅተኛውን ሶስተኛ ደረጃ ይዘዋል፡

## .በስዊዝ ኢትዮጵያውያን የተቃውሞ ሰላማዊ ሰልፍ ሊወጡ ነው

አውሮፓ በሚገኙ ኢትዮጵያውያን ስደተኞች ላይ እየደረሰ ያለው የመብት ረገጣ መባባሱንና በስዊዝ የኢትዮጵያ ስደተኞች የተቃውሞ ሰላማዊ ሰልፍ ለማድረግ ዝግጅት ላይ መሆናቸውን ገለጹ፡ በዙሪክ የስደተኞች ጊዜያዊ አስተባባሪ ኮሚቴ በተለይ ለጦቢያ እንደገለጸው በስዊዝ በሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ስደተኞች ላይ የሚደርሰው እንግልት እየተባባሰ በመምጣቱ ሳቢያ በጄኔቭ ከተማ በሚገኘው የተባበሩት መንግሥታት ጽ/ቤት ፊት ለፊት የተቃውሞ ሰልፍ ለማድረግ በዝግጅት ላይ መሆናቸውን አስታውቋል፡ እንደ አስተባባሪው ኮሚቴ መግለጫ ከሆነ ከዚህ በፊትም በተለያዩ ካንቶኖች ወይም ቦታዎች በሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ላይ ከሥራ መፈናቀልና ከሚኖሩበት ቤት በማስወጣትና በማሰር ግፍ ሲፈጸምባቸው መቆየቱን አውስቶ ይህን ኢ-ሰብዓዊ ድርጊት በመቃወም አንዲት ኢትዮጵያዊት ለሃያ አንድ ቀናት የረሃብ አድማ ማድረጓንና በአሁኑ ወቅትም በሕክምና እርዳታ ሕይወቷ ሊተርፍ እንደቻለ ገልጿል፡ የስዊስ መንግሥት እየወሰደ ያለው እርምጃ በተባበሩት መንግስታት የጸደቀውን የጄኔቫ እና የቪዬና ኮንቬንሽን የስደተኞች ሰብአዊ መብት እንደሚጻረር ያመለከተው ኮሚቴ ይህን ሕገ ወጥ እርምጃ በመቃወም በዓይነቱ ታላቅ የሆነ ሰላማዊ ሰልፍ ለማድረግ በዝግጅት ላይ መሆኑን አስታውቋል፡ ይህ በዚህ እንዳለ በኬንያ በሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ስደተኞች ላይ ሰሞኑን በተደረገው አሰሳ በርካታ ኢትዮጵያውያን ታፍሰው መታሰራቸውን ለማወቅ ተችሏል፡ ከናይሮቢ የደረሱን መረጃዎች እንዳመለከቱት ከስደተኞች መጠለያ ውጭ በሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ላይ በተካሄደው አፈሳ በርካታዎቹ ፖሊስ ጣቢያ የታሰሩ ሲሆን ከነዚህ ውስጥም በስደት ያሉ የነፃው ፕሬስ አባላት እንደሚገኙበት ጨምረው ገልጸዋል፡

## አውስትራሊያ ከኢትዮጵያ ዕዳ ስድስት ነጥብ አንድ ሚሊዮን ዶላሩን ቀነሰች

ኢትዮጵያ ለአውስትራሊያ መክፈል ከሚጠበቅባት ዕዳ ውስጥ ስድስት ነጥብ አንድ ሚሊዮን ዶላሩን የአገሪቱ መንግሥት ሙሉ በሙሉ መሰረዙን አስታወቀ፡ የአውስትራሊያ መንግሥት እንደገለፀው፤ ኢትዮጵያ የዓለም ባንክና ዓለም አቀፉ የገንዘብ ድርጅት ያወጡትን መስፈርት አሟልታ ተገኝታለች፡ ሮይተርስ ከካንቤራ እንደዘገበው፤ በሁለቱ ዓለም አቀፍ የገንዘብ ተቋማት መስፈርት መሰረት የዕዳ ጫና ያለባቸው ደሃ አገሮች ከበለፀጉ አገሮችና ከአበዳሪ ተቋማት የወሰዱት ገንዘብ የሚሰረዝላቸው በማሕበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና በፖለቲካዊ የፖሊሲ አቅጣጫዎች ሥርነቀልና መሰረታዊ ለውጥ ማምጣታቸው ሲረጋገጥ ነው፡ ደሃ አገሮች እነዚህ አስፈላጊ የለውጥ አቅጣጫና መስፈርት ማሟላታቸው በተቋማቱ ከተረጋገጠ ከአበዳሪ ተቋማትም ሆነ ከበለጸጉት አገሮች በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ቀደም ሲል የወሰዱት ብድር ተሰርዞ ለትምህርት፣ ለጤናና ለድህነት ቅነሳ ፕሮግራም እንቅስቃሴ እንዲያውሉት ይደረጋል ብሏል፡ ኢትዮጵያም ለዕዳ ቅነሳ የተቀመጠውን መስፈርት በተገቢው መንገድና በቁርጠኝነት ለማሟላት በመቻሏ የዕድሉ ተጠቃሚ እያደረጋት መሆኑን ዘገባው አመልክቷል፡

## *ኢትዮጵያ በሶማሊያ ህገ-ወጥ ንግድ በዓመት ከ162 ሚሊዮን ዶላር በላይ ታጣለች*

ኢትዮጵያ በኮንትሮባንድ የበግ፣ የፍየል፣ የቀንድ ከብት፣ ከግመልና ከጫት ንግድ በሶማሊያ በኩል በሚደረግ ህገ-ወጥ ንግድ ከ 162 ሚሊዮን ዶላር ታጣለች፡ የጅጅጋ ንግድ ም/ቤት አባል ለተለያዩ የመንግስት ከፍተኛ ኃላፊዎች በጻፉት ደብዳቤ እንደገለጹት ኢትዮጵያ የጠቀሱትን ዶላር ያህል በዓመት ታጣለች፡ በየዓመቱ ከበርበራ ወደብ የሚወጣው የበግና ፍየል ቁጥር 3 ሚሊዮን እንደሚደርስና ከዚህም ውስጥ 2 ሚሊዮን ያህሉ በህገ ወጥ መንገድ እንደሚወጣ ገልጿል፡ አገሪቱ በኮንትሮባንድ ሳቢያ ከበግና ፍየል ከ 80 ሚሊዮን ዶላር በላይ እንደምታጣ ደብዳቤው ያስረዳል፡ በበርበራ በኩል ከሚወጣው የሥጋ ከብት 80 በመቶ በላይ የሚሆነው በኮንትሮባንድ እንደሚወጣ ደብዳቤው ጠቁሟል፡ በዚህ ሳቢያ አገሪቱ ከ 24 ሚሊዮን ዶላር በላይ እንደምታጣ አስታውቋል፡ በየዓመቱ ከኢትዮጵያ በተጠቀሰው መንገድ 16 ሺህ ግመሎች ሲወጡ ከ 11 ሺህ በላይ የሚሆኑት በህገወጥ መንገድ የወጡ ናቸው፡ አጠቃላይ ዋጋውም ከ 44 ሚሊዮን ዶላር በላይ መሆኑን ለመንግሥት ባለሥልጣናት የተጻፈው ደብዳቤ ያሳያል፡ በየቀኑ ድንበር አቋርጦ ወደ ሶማሊያ የሚገባው ጫት ሃብት መጠን 50 ሺ ኪሎ የሚገመት ሲሆን ይህም መጠን ሕጋዊ በሆነ መንገድ እንዲወጣ ቢደረግ በንግድ ሕግ መሠረት የአንድ ኪሎ ጫት ዋጋ 3 የአሜሪካን ዶላር በመሆኑ አጠቃላይ ሂሳቡ ሲሰላ ከ 54 ሚሊዮን ዶላር ውስጥ 32 ሚሊዮን ያህሉን እንደምታጣ ደብዳቤው ገልጿል፡ በዚሁ መሰረት አገሪቱ በቀን 150 ሺ ዶላር፣ በወር 4 ሚሊዮን 5 መቶ ሺ ዶላር እንደምታጣና መንግሥትም ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥቶ መከታተልና ሕጋዊ ንግድ እንዳይኖር ጥረት እንዲያደርግ የምክር ቤቱ አባል የመንግሥት ኃላፊዎች ጠይቀዋል፡ የም/ቤቱ አባላት ጥያቄዎቻቸውን ሲያቀርቡ የተጠቀሙባቸው አሃዞች በአካባቢው የተደረጉ ጥናቶችን መሰረት ያደረጉ ናቸው፡ የአሃዝ መረጃዎቹ ንግድ ም/ቤቱ በመረጃነት የመዘገባቸው ናቸው፡

## *ኢትዮ-ኬኒያ ድንበር ግድያና አፈና እየተባባሰ መምጣቱ ተገለፀ*

የኢትዮጵያ መንግስት ወታደሮች ሳይሆኑ አይቀሩም የተባሉ ወራሪዎች የኬኒያን ድንበር ጥሰው በመግባት አንድ ፖሊስ ገድለው ሁለት ሰዎችን አፍነው መውሰዳቸውን ዘ ኔሽን የተባለው የኬኒያ ጋዜጣ ዘገበ፡ ይህንኑ ወረራ ተከትሎ የኬኒያ መንግስት በድንበር አካባቢዎች ባደረገው ፍተሻ በኬኒያ ሞያሌ ኤ.ኬ 47 የተባለ መሣሪያ የታጠቀ ኢትዮጵያዊ የተያዘ ሲሆን፤ ከድንበር ጥሰቱ ጋር በተያያዘ ጥያቄ እየተደረገበት እንደሆነ ተገልጿል፡

የኬኒያ ከፍተኛ የፖሊስ ባለሥልጣን ለጋዜጣው እንደገለጹት «የኢትዮጵያ መንግስት ወታደሮች ግድያውን ፈፅመው የፖሊስ ረዳቱን ይዘው ጠፍተዋል፡ እስካሁን ድረስም ረዳቱ የት እንደደረሰ አይታወቅም» ሲሉ ተናግረዋል፡ የፖሊስ ከፍተኛ ባለሥልጣናት ጨምረው እንደገለፁት የፖሊስ መኮንኑ ሊገደል የቻለው ታጣቂዎቹ አፍነው ሊወስዱት ሲሞክሩ ለመሄድ ባለመስማማቱ እንደሆነ ገልፀዋል፡ የኬንያ መንግስት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትርና የኬኒያ ምስራቃዊ ግዛት አስተዳዳሪ በጋራ ባወጡት መግለጫ አጠቃላይ የደረሱበትን ስምምነት ለኢትዮጵያ መንግስት ከፍተኛ ባለሥልጣናት የላኩ መሆናቸው ተገልጿል፡ የኬኒያ መንግስት ከፍተኛ የፖሊስ መኮንን የተያዘውን የኢትዮጵያ ወታደር በተመለከተ «ወታደሩ በቁጥጥራችን ስር ነው፡ ለምንና እንዴት ወደ ኬኒያ እንደገባ እየተጠበቀ ነው፡ ከገዳዮቹ ጋር የተባበረ ከሆነ ወደ ፍርድ እናቀርበዋለን» ሲሉ ገልፀዋል፡ የድንበር ጠባቂ ፖሊሶችና የፖሊስ ኃይሉ የድንበር አካባቢውን በንቃት እየጠበቀ መሆኑ ተገልጿል፡ እንደሚታወሰው ከሁለት ሳምንት በፊት እኚሁ ድንበር ጥሶ የገባው ኃይል በኬንያ የድንበር አካባቢ ነዋሪዎች ላይ ጥቃት መሰንዘሩ ይታወሳል፡

## ብራድ ፒት ለኤድስ ህመምተኞች እርዳታ ሊያሰባስብ ነው

በኢትዮጵያ የሚካሄደውን የፀረ ኤድስ እንቅስቃሴ ለማየት ባለፈው ሳምንት አርብ ወደ አዲስ አበባ መጥቶ የነበረው ታዋቂው የፊልም ተዋናይ ብራድ ፒት ለኤድስ ህመምተኞች የገንዘብ ድጋፍ እንዲያሰባስብ ቃል ገባ፡ «ማፍቀር ነው መሰልጠን» የተሰኘውን የዘፈን ክሊፕ እንደወደደው ተናግሯል - ፒት፡ «ማፍቀር ነው መሰልጠን» የተሰኘው የዘፈን ክሊፕ ስለ ኤድ አይ ቪ ኤድስ ግንዛቤን ለማሳደግ እንደተጠቀመ መስማቱን የገለፀው ብራድ ፒት፤ የዘፈን ክሊፑን ቅዳሜ ምሽት በማኩሽ ጋላሪ ከተመለከተ በኋላ አድናቆቱን ገልጿል፡ በፋሚሊ ኸልዝ ኢንተርናሽናል በአድማስ አድቨርታይዚንግ የረዥም ጊዜ ጥናት አማካኝነት በተሰራው የዘፈን ክሊፕ ላይ በነጻ የተሳተፉ አርቲስቶችንም አመስግኗል - አሜሪካዊው ብራድ ፒት፡ ተዋናዩ እዚህ አዲስ አበባ በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ለኤድስ ህመምተኞች የተጀመረውን የቤት ለቤት እንክብካቤ ከጐበኘ በኋላ በእንክብካቤው የሚሳተፉ የዕድር አባላትንና የክፍለ ከተማውን ሃላፊዎች ማነጋገሩን የህይወት የኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያ ቢሮ ሃላፊ ለአዲስ አድማስ ገልፀዋል፡ ብራድ ፒት በሰጠው አስተያየት በተለያየ የሙዚቃ ስልት የሚያቀነቅኑ ድምፃውያን በአንድ ባንድ እንደሚሰራ ቡድን ተቀናጅተው ድንቅ ሥራ ማውጣታቸው እንዳስገረመው መናገሩን በምሽቱ ከነበሩ አርቲስቶች ለማወቅ ተችሏል፡ ከወጣት ኢትዮጵያውያን አርቲስቶች ጋር እራት ሲበላ፣ ፎቶ ግራፍ ሲነሳና የዘፈን ክሊፑን ሲመለከት የቆየው ፒት እፁብ ድንቅ ነው! ሲል ማምሸቱን የተናገሩት አርቲስቶች ሥራቸው በዝነኛው የፊልም አክተር መደነቁ እንዳስደሰታቸው ለአዲስ አድማስ ገልጸዋል፡ ብራድ ፒት ባለፈው ሰኞ ሌሊት ወደአገሩ ከመመለሱ በፊት ላሊበላን መጐብኘቱ የታወቀ ሲሆን ለኤድስ ህመምተኞች የቤት ለቤት እንክብካቤ እንዲሻሻልና የእድሜ ማራዘሚያ መድኃኒት የሚውል የገንዘብ እርዳታ ማሰባሰብ ዘመቻ ይጀምራል ተብሏል፡

## Mandela …

*(Continued from page 1)*

street is called Nelson Mandela Street, and the organisation is called Nelson Mandela Panel Beaters, we're not too worried," he said. Mr Mandela wants to register not only his own name, but also his clan name "Madiba", his Xhosa name "Rolihlahla", and his prison number. The number 46664 is the name of Mr Mandela's Aids awareness campaign, and was used to publicise a huge pop concert for the cause in Cape Town last year. "Since the launch of the 46664 campaign in Cape Town, people, through the popularity of the events, saw a commercial opportunity," Mr Scholtz said. They included a company minting gold coins with Mr Mandela's image, Investgold ICC, which had registered 46664 as a phone number. Mr Scholtz said the firm had agreed to give up the number after being approached. A dispute over whether the minting can continue is still ongoing, however. A lawyer for the foundation, Don MacRobert, estimates it has lost

**CECA Memberships**

**stand at 412**

## New cave found in Ethiopia's Keffa zone

**ADDIS ABABA, November 12 (ENN**

Two American archaeologists said they have discovered an ancient cave in Tello woreda, Keffa zone of Ethiopia, Ethiopian News Agency (ENA) reported.

The cave, found in the Southern Nations, Nationalities and Peoples State, is estimated to be 28-30 million years old.

The researchers said the cave has two entrances. The width and length of the cave is 80 and over 100 meters respectively while the height is four meters, according to the report.The archaeologists, who are conducting a research in the woreda, said they have found ash and stone tools in the cave, indicating people used to live there.

Ato Workagegnehu Kassa, head of the zonal Culture and Information Department said studies will continue in the woreda. There are many caves in Tello woreda, ENA said.

## በሳውዲ ኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች እየታሰሩ ነው

ነዋሪነታቸውን በሳዑዲ ያደረጉና በእምነታቸው ክርስቲያን የሆኑ በርካታ ኢትዮጵያውያንና የሌሎች ሃገር ዜጎች በሳዑዲ የፀጥታ ኃይሎች የመታሰርና የመገረፍ እርምጃ እየተወሰደባቸውና እንዲሁም ልዩ ልዩ ስቃይ እየደረሰባቸው መሆኑን «ኤሽያ ኒውስ» ዘገበ፡ በአሁኑ ወቅት በሪያድ የሚገኙ እስር ቤቶች በክርስትና እምነት ተከታዮች መጨነቃቸውን የዘገበው የዜና አውታሩ በዚህም ምክንያት በሳዑዲ የሚኖሩ ከ8 ሚሊዮን በላይ የውጭ ዜጎች በፍርሃት እየተናጡ እንደሚገኙ አክሎ አስታውቋል፡ እንደ የዜና አውታሩ ዘገባ በቅርቡ እንኳን አስር የክርስትና እምነት ተከታዮች የሆኑ ኢትዮጵያውያንንና ኤርትራውያን በአንድ ቤት ውስጥ ሲጸልዩ በሪያድ ፖሊስ ተይዘው በእስር ቤት በመማቀቅ ላይ እንደሚገኙ ሲታወቅ ፖሊስ ለመታሰራቸው የሰጠው ምክንያት ደግሞ አልኮል ሲጠጡ ተገኝተዋል የሚል ነው፡ ከአንድ ዓመት በፊት ሦስት የክርስትና እምነት ተከታይ የሆኑ ኢትዮጵያውያን ጅዳ በሚገኘው በብሬመን ወህኒ የደረሰባቸውን በእስር መንገላታትና መገረፍ «ለዓለም አቀፍ ክርስቲያን ኮንሰርን» ጽ/ቤት በደብዳቤ ማስታወቃቸውን ያስታወሰው የዜና አውታሩ እነዚሁ ኢትዮጵያውያን ውንጀላቸው ሆኖ የተገኘው በእምነታቸው ክርስቲያን መሆን ብቻ ነበር ብሏል፡ ይኸው «ውንጀላቸው» ስድስት ወር በወህኒ ቤት እንዲያሳልፉ እንዳደረጋቸውም «ኤሽያን ኒውስ» አክሎ አስታውቋል፡

## ባንኮች ከ100 ሺህ ዶላር በላይ ተጭበረበሩ

ከቅርብ ግዜያት ወዲህ በኢትዮጵያ ሀሰተኛ ዶላሮች መሰራጨታቸው የታወቀ ሲሆን፣ በካውንተር ፊት የማይደረስባቸው መሆኑ ደግሞ ጉዳዩን አወሳስቦታል፤ በዚህም ሳቢያ የሀገሪቱ ባንኮችም በብዛት መጭበርበራቸውን መረዳት ተችሏል፡

በሀገሪቱ «ፎርጂድ»ዶላሮች መሰራጨታቸው የታወቀ ባንኮቹ የውጭ ምንዛሪያቸውን አሜሪካ ወደሚገኘው ኮሚርዝ ባንክ በላኩበት ወቅት መሆኑንም የብሔራዊ ባንክ ምንጮች ገልጸዋል፡ እዚህ ሀገር ውስጥ የተሳሳቱ ገንዘቦችን ለመለየት የሚያገለግለው ማሽን ሀሰተኞቹን ዶላሮች መለየት ባለመቻሉ፣ ዶላሮቹ ሀሰተኛ መሆናቸው የታወቀ እጅግ ዘመናዊ በሆነ ማሽን አሜሪካ ውስጥ ከተፈተሹ በኋላ ነው ተብሏል፡

በዚህም ሳቢያ ከሁለት የግል ባንኮች 140 ሺ እና 77 ሺህ ሀሰተኛ ዶላር እንደተገኘም ተመልክቷል፤ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክም በመቶ ሺህዎች የሚቆጠር ሀሰተኛ ዶላር እንደተገኘም ንጮቹአብራርተዋል፤ ሀሰተኛ ዶላሮቹ በሀገሪቱ ባሉት ካውንተር ፊቶች የማይደረስባቸው በመሆኑ፣ በባንክም ሆነ በጥቁር ገበያ የዶላር ምንዛሪ ማግኘት አስቸጋሪ እንደሚሆን ታምኖበታል፡ ሀሰተኛዎቹ ዶላሮች ከአለፈው ጥቅምት ወር በስፋት መሰራጨታቸውንም የባንክ ምንጮች ገልፀዋል፡

## የጋሽ አበራ ፕሮጀክት በእንግሊዝ ተሸለመ

በአዲስ አበባ ከተማ ከፍተኛ የፅዳት ስራን በማከናወን ላይ የሚገኘው የጋሽ አበራ ሞላ ፕሮጀክት፣ አለም አቀፍ የወርቅ ሽልማት አገኙ፡

ፕሮጀክቱ በእንግሊዝ ፓርላማ ውስጥ ኖቬምበር 4 በተከናወነው ስነ-ስርዓት ተሸላሚ የሆነው «በግል ፍቃደኝነት ታላቅ ስራ የሰሩ» በሚል ነው፡ የፕሮጀክቱ መስራች አርቲስት ስለሺ ደምሴና አስተባባሪው ተካሁን ባሻ፣ ትናንት ሽልማቱን ምክንያት በማድረግ በራስ መኮንን ድልድይ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ ፣ ፕሮጀክቱ ለሽልማቱ ዕጩ ሆኖ እንዲወዳደር ያደረገው በለንደን የኢትዮጵያ ኤምባሲ መሆኑን ተናግረዋል፡ አንድ ሺህ ተወዳዳሪዎች በእጩነት ባቀረቡበት ስነ ስርዓት ላይም፣ ኢትዮጵያ በሁለት አካላት በወርቅና ብር ለመሸለም መቻሉን አርቲስት ስለሺ ደምሴ ገልጿል፡ በወርቅ ከኢትዮጵያ ተሸላሚ የሆነው የጋሽ አበራ ሞላ ፕሮጀክት ሲሆን፣ በብር ደግሞ የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ተሸላሚ ሆኗል፡ አርቲስ ስለሺ ደምሴ፣ «ባለፈው ጊዜ ያከናወነው የፅዳት እንቅስቃሴ የአዲስ አበባን መልክና ገፅታ ቀይሮታል፡ ደስ የሚለው ነገር ይህ እንቅስቃሴ ለሌሎችም ክልሎች አርአያ ሆኖ በየክፍለሃገሩ ከፍተኛ የሆነ የጽዳት ስራ እየተከናወነ ነው፡ የእኛ የፅዳት ስራ ፕሮጀክትም በባንግላዲሽ፣ በሜክሲኮና ኬንያ እየተሰራበት ነው፡» ብሏል፡ በለንደን ከተማ «ሀውስ ኦፍ ኮመንስ» በተባለው ትልቅ ፓርላማ የተሰጠው ሽልማት የእኛ ብቻ ሣይሆን የመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ነው ያለው አርቲስ ስለሺ፣ «የፅዳት ስራውም ገና «ሀ» ተብሎ ተጀመረ እንጂ አላለቀም፡ ገና ብዙ ነገር መለወጥ አለበት» ብሏል፡ ይህ የጋሽ አበራ ሞላ ፕሮጀክት ከዚህ በፊትም የተባበሩት መንግስታት ሽልማትን ማግኘቱ በስነ-ስርዓቱ ላይ ተገልጿል፡

## *የኢትዮጵያ ስልክ ቁጥሮች ከ8 ወደ 10 ዲጂት ሊለውጥ ነው*

በአሁኑ ወቅት በስራ ላይ እየዋለ ያለው የስልክ ቁጥር አሰጣጥና አመዳደብ ለተጨማሪ መስመሮችና አዳዲስ አገልግሎቶች ቁጥር ለመስጠት ክፍተት የሌለው በመሆኑ በአዲስ የስልክ ቁጥር አመዳደብ እንደሚተካና በመላው ሀገሪቱ በአገልግሎት ላይ ያሉት ስልክ ቁጥሮችም በአዲስ ቁጥሮች እንደሚለወጡ የዝግጅት ክፍላችን ከኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኤጀንሲ ባገኘው መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡

በአሁኑ ወቅት በሀገሪቱ በስራ ላይ ያለው ስልክ ቁጥር የአካባቢ ኮድን ጨምሮ ባለ ስምንት ዲጂት መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን፣ ወደፊት በመላ ሀገሪቱ በስራ ላይ ሊውል የታቀደው ስልክ ቁጥር ባለ አስር ዲጂት መሆኑን ኤጀንሲው በትናንትናው ዕለት ለቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን ባለሥልጣኖች ይፋ ባደረገው ረቂቅ ፕላን ለማወቅ ተችሏል፡

በብሔራዊ ደረጃ በስራ ላይ ሊውል የታቀደው ባለ 10 ዲጂት ቁጥር አሁን በስራ ላይ ያለውን ባለሁለት ዲጂት area code ወደ ሦስት ዲጂት ከፍ የሚያደርገው ሲሆን፤ በተመሳሳይ ባለሁለት ዲጂት የሆነው ወደ ሦስት ዲጂት የሚቀይረው ይሆናል፡ በአሁኑ ሰዓት አንድ ተጠቃሚ ባለበት አካባቢ (area code) ወደሚገኝ ስልክ ለመደወል የአካባቢውን ኮድ ቁጥር አካቶ መደወል የማያስፈልገው ሲሆን (ማለትም አዲስ አበባ ሆኖ በዛው ከተማ ወደሚገኝ ስልክ ለመደወል የአዲስ አበባ area code (01) ማካተት የማያስፈልግ ሲሆን) ወደፊት ሊቀየር በታሰበው ባለ 10 ዲጂት ስልክ ቁጥር አጠቃቀም ተቃዋሚው የሚደውልበት ቦታ የትም ይሁን የትም አስሩንም ዲጂቶች መደወል ይኖርበታል፡ አሁን ባለ አስር ዲጂት የስልክ ቁጥር በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ በስራ ላይ እንደሚውል የሚገልፀው ረቂቁ ፕላን አሁን በስራ ላይ ያለ ባለስምንት ዲጂት ስልክ ቁጥር ከአገልግሎት ውጪ እንዲሆን ከመደረጉ በፊት ለስድስት ወር ያህል ከአዲሱ ስልክ ቁጥር አጠቃቀም ጋር ጎን ለጎን በስራ ላይ እንደሚቆይ ያመለክታል፡ ይኸው አዲሱ የስልክ ቁጥር አመዳደብ ለተጨማሪ መስመሮች፣ አዲስ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎቶችና (በአሁን ሰዓት በሀገሪቱ ብቸኛው የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሰጪ ቴሌ ቢሆንም) ከቴሌ ውጭ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ለሚሰጡ አካላት ወዲያው አዲስ ስልክ ቁጥሮችን ለመስጠት የሚያስችልና ወደፊትም በስራ ላይ ሊውል ይችላሉ ተብለው ለሚገመቱ አዳዲስ አገልግሎቶች ተጠባባቂ ቁጥሮች ይይዛል እንደ መረጃው፡ አዲሱ አስር ዲጂት ስልክ ቁጥር በስራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልገውን የተለያዩ ወጪዎች ከቴሌና ከተጠቃሚው ህብረተሰብ የሚወጣ ይሆናል፡

## Encyclopaedia Aethiopica published

The first volume of an Encyclopaedia that covers a large scope of subjects on Ethiopia's culture, language and general data has been published, the Amharic weekly Nation reported on Saturday.

The editors of the Encyclopaedia also plan to compile four additional volumes, the newspaper said.

The major themes included in the Encyclopaedia are basic data, history, language, anthropology, archaeology, literature, religion and art.

Ato Shiferaw of Addis Ababa University and Mr. Wolbert Smidt of Hamburg University announced recently at German Cultural Institute that the Encyclopaedia was organized and published by Hamburg University, Institute of African and Ethiopian Studies.

400 international community of scholars working in various scientific fields co-operated on creating the index book that gives information not only on Ethiopia but also on large territories of the Horn of Africa, including Eritrea, Djibouti and Somalia.

# ማስታ˜ቂያ

በካልጋሪ የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማህበር ከ400 በላይ የተመዘገቡ አባላት ቢኖሩትም ለማህበሩና ለአባላት ጠቃሚ የሆኑ ውሳኔዎች በሚተላለፉባቸው ስብሰባዎች ላይ የሚገኙት ቁጥር እጅግ አነስተኛ ነው፡፡ ይህ ሁኔታ ተሻሽሎ የማህበሩ አባላት በበቂ ቁጥር ተገኝተው መሳተፍ የሚችሉበት መንገድ ቢታቀድ ለማህበሩ መጠንከር ጉልህ አስተዋፅኦ ይኖረዋል በሚል እምነት አባላት በስብሰባዎች ላይ የማይገኙበትን ምክንያት ጠይቆ በማግኘት የመፍትሄ ሃሳብ ለመጠቀም በበጎ ፈቃድ በተነሳሱ የኮሚኒቲው አባላት ገለልተኛ ኮሚቴ ተቋቁሟል፡፡

ገለልተኛ ኮሚቴው አብዛኛው የማህበሩ አባላት በስብሰባ ላይ የማይገኙበት የየራሳቸው ቅሬታና ገንቢ ሃሳባቸው በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ትኩረት ተሰጠቶት እርምጃ ቢወሰድበት ማህበሩ ሊጠናከር እንደሚችል እምነት አለው፡፡ ገለልተኛ ኮሚቴው ጥናቱን የሚያካሂደው የኮሚኒቲው አባላት ለሆኑ ሁሉ ስልክ በመደወልና ኢሜይል በመላክ ሲሆን አባላት ይህን በጎ ሃሳብ አውቃችሁ ከጊዜያችሁ ላይ 5 ደቂቃ መስዋእት በማድረግና በግልጽ ሃሳባችሁን በመስጠት እንድትተባበሩት ኮሚቴው በትህትና ይጠይቃል፡፡

## *የታላቁ የስፖርት ሰው የክቡር አቶ ይድነቃቸው ተሰማ ሐውልት ተመረቀ*

በቅዱስ ጊዮርጊስ ስፖርት ማህበር ክበብ ቅጥር ግቢ የተሰራው የታላቁ የስፖርት ሰው የክቡር አቶ ይድነቃቸው ተሰማ የመታሰቢያ ሐውልት ተመረቀ፡ የስፖርት ማህበሩ የህዝብ ግንኙነት ክፍል እንደ ገለጸው አቶ ኃይለ አድምጤ የተባሉ ግለሰብ በ 12 ሺህ ብር ያሰሩት ሐውልት በሚመረቅበት ሥነ ሥርዓት ላይ የታላቁ የስፖርት ሰው ባለቤት ወ/ሮ በዛብሽ ተ/ማርያም፥ ልጃቸው አቶ ታደለ ይድነቃቸው፥ ቤተሰቦቻቸውና ጥሪ የተደረገላቸው ታላላቅ ሰዎች ይገኛሉ ተብሎ ይጠበቃል፡ ከታዋቂው ባለቅኔ ከነጋድራስ ተሰማ እሸቴና ከወ/ሮ ሙላት ገብረየስ መስከረም 1 ቀን 1914 ዓ.ም በጅማ ከተማ የተወለዱት አቶ ይደነቃቸው ዘመናዊ ስፖርት በኢትዮጵያ እንዲስፋፋ፥ ለአፍሪካውያን ንብረትና ጥንካሬ የሚበጅ የአፍሪካ እግር ኳስ ኮንፌዴረሽን እንዲቋቋም፥ ከደቡብ አፍሪካ ስፖርት የዘርም መድልዎ እንዲወገድ፥ የአፍሪካ ኮታ በዓለም ዋንጫ እንዲጨምር በማድረግ አገርንና መላውን አፍሪካ የሚያኮራ ታላቅ ሥራ አከናውነዋል፡ በኢትዮጵያ እግር ኳስ ታሪክ ቀዳሚ ቦታ ያላቸው ታላቁ የስፖርት ሰው በ 1928 ለተቋቋመው አንጋፋው የቅዱስ ጊዮርጊስ ቡድንና ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ተጫውተዋል፡ በአሠልጣኝነት ሠርተዋል፡ የእግር ኳስ ሕጐችን ወደ አማርኛ በመተርጐምና በማስተማር በርካታ ኢንተርናሽናል ዳኞችን አፍርተዋል፡ እስከ ዕለተ ሞታቸው ለስፖርት ዕውቀታቸውና ጉልበታቸውን ያዋሉት አቶ ይደነቃቸው ለኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴረሽን መመሥረት ከፍተና መስዋዕትነትን ከፍለዋል፡ በ 1952 የኢትዮጵያ ስፖርት ኮንፌዴሬሽን ዋና ፀሀፊ፥ በ 1955 በዋና ዳይሬክተርነት ማዕረግ የኢትዮጵያ ስፖርት ኮንፌዴሬሽን ዋና ጸሐፊ፥ በ 1960 ረዳት ሚኒስትር፥ በ 1964 ምክትል ሚኒስትር ከ 1968 እስከ 1973 የስፖርት ኮሚሽነር በመሆን አገልግለዋል፡ በአፍሪካ እግር ኳስ ኮንፌዴሬሽን መስራችነት የሚታወቁት ታላቁ የስፖርት ሰው ከ 1964 እስከ 1972 የኮንፌዴሬሽኑ ምክትል ፕሬዚዳን

## ኃይሌ ገብረ ሥላሴ በቅርቡ ወደ ውድድር ለመመለስ አቅዷል

ኃይሌ ገብረሥላሴ በእግሩ ላይ የቀዶ ህክምና ባደረገ በአጭር ጊዜ ጤንነቱ በፍጥነት በመሻሻሉ በቅርቡ ወደ ውድድር ለመመለስ እየተዘጋጀ መሆኑን ገለፀ፡ ከሦስት ወራት በፊት የደረሰበትን ከባድ የእግር ህመም ተቋቁሞ በአቴንስ ኦሎምፒክ ከተወዳደረ በኋላ ቀዶ ህክምና ያደረገው ኃይሌ በዓለም አቀፉ አትሌቲክስ ፌዴሬሽኖች ማህበር ድረ ገፅ ላይ በሰጠው አስተያየት፤ ጤንነቱ በአጭር ጊዜ ውስጥ ይሻሻላል ብሎ እንዳልጠበቀና ሁኔታውም ከእርሱም አልፎ ሐኪሞቹንም እንዳስገረመ ገልጿል፡ ኃይሌ እንዳስረዳው፤ በጥር ወር የጤንነቱ ሁኔታ በዚሁ የሚዘልቅ ከሆነ በየካቲት ወር መጨረሻ አካባቢ የመጀመሪያ ውድድሩን ያደርጋል፡ ቀዶ ህክምና ከተደረገለት ከሦስት ሳምንት በኋላ ቀለል ያለ የቤት ውስጥ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ መጀመሩንና በአሁኑ ጊዜ በቀን ለአንድ ሰዓት ያህል በመካከለኛ ፍጥነት የጐዳና ላይ ልምምድ እያደረገ መሆኑን ኃይሌ አመልክቷል፡ ኃይሌ በማራቶን ላይ እንደሚያተርኩር ቀደም ሲል መግለጹ የሚታወስ ቢሆንም በየካቲት መጨረሻም የሚወዳደርበትን ርቀት አላስታወቀም፡

## *ይድነቃቸው ተሰማ ....*

አገልግለዋል፡ በአፍሪካ እግር ኳስ ኮንፌዴሬሽን መስራችነት የሚታወቁት ታላቁ የስፖርት ሰው ከ 1964 እስከ 1972 የኮንፌዴሬሽኑ ምክትል ፕሬዚዳንት ከ 1972 እስከ 1987 ፕሬዚዳንት በመሆን ከመሥራታቸውም በላይ የአፍሪካ ስፖርት ምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴ አባልና የአፍሪካ ኦሊምፒክ ኮሚቴዎች ማህበር የክብር ፕሬዚዳንት ነበሩ፡ ለአፍሪካ ለዓለም ባበረከቱት ከፍተኛ አስተዋጽኦ በተለያዩ አገሮችና ድርጅቶች ከፍተኛ ሽልማቶችን ያገኙት አቶ ይድነቃቸው ተሰማ የፊፋ ፕሬዚዳንት ይሆናሉ ተብሎ ሲጠበቅ በማይቀረው ሞት ነሐሴ 13 ቀን 1979 ዓ.ም ተሸነፉ፥ ፊፋ ሰኔ 24 ቀን 1980 ዙሪክ ላይ ባደረገው ስብሰባ የድርጅቱን የመጨረሻ ሽልማት ማለትም «የላቀ አገልግሎት የወርቅ መዳሊያ» በተጨማሪም ካፍ አርባኛውን የምሥረታ በዓሉን በመስከረም ወር 1980 በካይሮ ሲያከብር «የኮንፌዴሬሽኑ የላቀ አገልግሎት ልዩ የወርቅ መዳሊያ» ለማይሞተው ሥራቸውና ስማቸው ሸልመዋል፡ የሞሮኮው ንጉሥ ሐሰን ካዛብላንካ ላይ የሚገኝ ታላቅ ስታዲየም «ይድነቃቸው ስታዲየም» ተብሎ እንዲሰየም መጋቢት 3 ቀን 1980 ፈቅደዋል፡ በበቀሉባትና ባገለገሏት ኢትዮጵያ ለአሥራ ስምንት አመታት ተረስተው ከቆዩ በኋላ መንግስትና ሕዝብ ሳይሆን ግለሰብ ያሠሩላቸው የመታሰቢያ ሀውልት ዛሬ ይመረቃል፡ በአንድ ወቅት የስፖርት ፖሊሲን አስመልክቶ አዋሳ ላይ በተካሄደ ሲምፖዚየም «ባለፉት ሥራዓቶች ስፖርቱ በደመነፍስ ነበርይ የሚመራ» በማለት የታላቁን የስፖርት ሰው ታላቅ ሥራ ያጣጣሉ በአሁኑ ወቅት የቅዱስ ጊዮርጊስ ስፖርት ማኅበር ዋና ሥራ አስኪያጅ በመሆናቸው ዛሬ የአቶ ይድነቃቸው ሕያው ሥራ መታሰቢያ ከሆነው ሐውልት ጋር ይፋጠጣሉ ተብሎ ይጠበቃል፡

# *Seasons Greetings!*

*I want to wish you and your family all the joy and serenity that comes with this wonderful time of the year. May all your hopes and dreams for the coming year are fulfilled!*

*I would like to especially thank each and every one of my clients, past and present, sincerely. I am grateful for allowing me to assist you with the biggest investment you will probably make in your lifetime. I appreciate the confidence you have put in me. May you continue to prosper for many more years to come!*

**መልካም ዓውደ ዓመት**

**በተለይም ባለፈው ጊዜና አሁንም ቤት በመግዛትና በመሸጥ ሂደት ውስጥ በአገልግሎቴ ተማምናችሁ አብሬኣችሁ እንድሰራ እድሉን ለ ሰጣችሁኝ ሁሉ ምስጋናዬን እያቀረብኩ፣ መጪው ወቅት የጤንነት፣ የሰላምና የብልፅግና እንዲሆንላችሁ እመኛለሁ።**

**መጪው የበዓላት ወራት የደስታና የ ብልፅግና ወቅት እንዲሆንላችሁ ምኞ ቴን እገልፃለሁ።**

MaxWell

TAD MULUGETA
Real Estate Agent
MaxWell Classic Realty
*An independent member broker*

#525, 500 Country Hills Blvd. NE
Calgary, Alberta T3K 4Y7
Bus: (403) 226-9318
Fax: (403) 226-8566
Cell: (403) 815-4394
Email: tmgeta@shaw.ca





Copyright © 2004 CECA